የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
Food, Beverage and Pharmaceutical Industry Development Institute

ቁጥር 12/72
Ref. No
ቀን 19/11/11
Date

ለኢትዮጵያ የታሸገ ዉኃና ለስላሳ መጠጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፦የታሸገ ዉኃ አምራቾች የአንገት ላይ ሽፋን (Neck Seal) እንዳይጠቀሙ ስለመከልከል

የኢትዮጵያ የታሸገ ዉሃና ለስላሳ መጠጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበር በታሸገ የዉኃ ምርት ላይ በተለምዶ የሚጠቀሙት የአንገት ላይ ሽፋን (Neck Seal) እንዲከለከል በሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም መንግስታዊና በዘርፉ የተሰማሩ አምራች ድርጅቶች በተገኙበት የፕሬስ ኮንፈረንስ ጠርቶ ከሐምሌ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የአንገት ላይ ሽፋንን መጠቀም እንዲያቆሙ ለአምራቾች የተላለፈዉን መልዕክት በተመሳሳይ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እቅድ ተይዟል፡፡

ከዚህ ጋር በተያዘ ከዚህ በፊት የተፃፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ፣ በታሸገ ዉሃ ላይ የአንገት ላይ ሽፋን መጠቀም እንዲቀር የተጠናዉን ጥናት በደብዳቤ እንድንገልጽላቸዉ በሐምሌ 03 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር EBSMIA 098/2019 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት የአንገት ላይ ሽፋን መነሳቱ የሚኖረዉን ጠቀሜታ ከአምራቾችና ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ጥናትና ዉይይት ተደርጓል፡፡ የአንገት ላይ ሽፋን እንዳይጠቀሙ መከልከሉ ጠቀሜታ ያለዉ መሆኑን በሚከተሉት ዋና ምክንያቶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ✓ የአንገት ላይ ሽፋን ባለመጠቀማቸዉ የአካባቢ ብክለትን ከመከላከል አንፃር ዋና አስተዋፅኦ ያለዉ በመሆኑ፤
- ✓ የአንገት ላይ ሽፋን በዉጭ ምንዘሬ የሚገዛ በመሆኑ ቢቀር የዉጭ ምንዘሬ (foreign currency) በማስቀረት ለአገራችን እድገት አስተዋፅኦ ስላለዉ፤
- ✓ ምርቶቹን አስመስሎ (forgery) ለመስራት ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ አስመስሎ መስራትን የሚያስቀር ስለሆነ፤
- ✓ የአንገት ላይ ሽፋን የተደረገዉ በተለምዶ እንጂ ሌላ ምንም አይነት የአስፈላጊነት/አስገዳጅነት ህጋዊ መሰረት እንደሌለዉና አላስፈላጊ በመሆኑ፤
- ✓ የአለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየዉ የአንገት ላይ ሽፋን በዉኃ ማሸጊያ ላይ የማይጠቀሙ በመሆኑ፤


ስልክ፡ +251 114701331 (ዋና ዳይሬክተር) ፋክስ +251114702507 ፖስታ፡ 46883
+251 114702502 (ህዝብ ግንኙነት)

- ✓ በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገራችን የሚመረቱት የለስላሳና የጁስ ምርቶች ላይ የማይጠቀሙ በመሆኑ፤
- ✓ በታሸገ ወኃ ጥራት ላይ ምንም የሚቀንሰዉ ደረጃ (Standard) ያለመኖሩ፤
- ✓ አቧራ ከመከላከል ይልቅ እንዲጠራቀም ምክንያት በመሆን፤
- ✓ የአንገት ላይ ሽፋን ባለመጠቀም ምርታማነትን እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑና በምርቱ ላይ አላስፈላጊ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዳይጨምር ስለሚረዳ ናቸዉ።

በመሆኑም የታሸገ ዉኃ አምራች ኩባንያዎች በዉኃ ማሸጊያ ላይ የሚጠቀሙትን የአንገት ላይ ሽፋን እንዳይጠቀሙ መደረጉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያለዉ መሆኑን ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም እና የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ከአምራቾችና ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ዉይይቶች ከስምምነት ላይ ተደርሷል።

ስለሆነም በታሸገ ዉኃ ማሸጊያ ላይ የሚደረገው የአንገት ላይ ሽፋን (Neck Seal/Sleeve) አምራቾች እንዳይጠቀሙ ለማድረግና ለተፈጻሚነቱም ከማህበሩ፣ ከአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እና ከኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በጋራ የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

በቀለ መኩሪያ
የምግብና መጠጥ ዘርፍ
ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን
- ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት (ምግብና መጠጥ ኢ/ል ዘርፍ)
- ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት (ኢንቨስትመንትና ቴክኖሎጂ ዘርፍ)

<u>ም/መ/ፋ/ኢ/ል/ኢ.</u>